የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 34
ADDIS ABABA April th, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፱/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/ ፪ሺ፲፪ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ……………………፲፪ሺ፬፻፺፱

## Content

Proclamation No.1189/2020

A Proclamation to Approve the State of Emergency Proclamation Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19 and Mitigate Its Impact Proclamation No. 3/2020. Page …………………………………………………..12499

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፱/፪ሺ፲፪

**<u>የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/ ፪ሺ፲፪ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀ በመሆኑ፤

ይህንኑ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያዚያ ፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄድው ስብሰባ የመረመረውና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፺፫(፫) መሠረት ያፀደቀው በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1189 /2020

**<u>A PROCLAMATION TO APPROVE THE STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION NO. 3/2020 ENACTED TO COUNTER AND CONTROL THE SPREAD OF COVID-19 AND MITIGATE ITS IMPACT</u>**

Since a state of emergency to counter and control the spread of COVID-19 and mitigate its impact has been proclaimed by the Council of Ministers on April 8th 2020;

Since this state of emergency proclamation has been considered and approved by the House of Peoples' Representatives on 10th 2020 in accordance with Article 93(3);

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፺፫(፫) እና ፶፭(፰) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩ . **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/ ፪ሺ፲፪ን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፱/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ስለማፅደቅ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ያወጀው የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ በዚህ አዋጅ ጸድቋዋል።

፫. **የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ**

፩) የኮቪድ-፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ መርማሪ ቦርዱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፺፫ (፯) የተመለከቱት ስልጣን ይኖረዋል።

፪) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቦርዱን አባላት ይሰይማል::

፬. **የቦርዱ ሰብሳቢ ሥልጣን እና ተግባር**

የቦርድ ሰብሳቢ፡-

፩) ቦርዱን ይመራል፣

፪) አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴውን በበላይነት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

፫) ለቦርዱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ይመድባል፣

፬) ቦርዱን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡



In accordance with the FDRE Constitution Articles 93(3) and 55(8), this state of emergency has been proclaimed.

1 . **Short Title**

This Proclamation may be cited as the A Proclamation 1189/2012 "A Proclamation to Approve the State of Emergency Proclamation Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19 and Mitigate Its Impact Proclamation No. 3/2020."

2 . **Approval of the State of Emergency Proclamation**

The state of emergency Proclamation enacted on 8th April 2020 to counter and control the spread of covid-19 and mitigate its impact, Proclamation No. 3/2020 is hereby approved.

3 . **A State of Emergency Inquiry Board**

1) A State of Emergency Inquiry Board having the Powers and Responsibilities provided under Article 93(6) of the FDRE Constitution is here by been established in relation to the Proclamation to Approve the State of Emergency Proclamation Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19 and Mitigate Its Impact.

2) The House of Peoples' Representatives shall assign seven members to serve in the inquiry Board.

4 .**Powers and Responsibilities of Chairperson of the Board**

The Chairperson of the Board shall;

1) Lead the Board;

2) Oversee and follow up the overall activities of the Board;

3) Assign support staff necessary for the activities of the Board;

4) Represent the board in its relation with third

parties.

**፭. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣን እና ተግባር**

የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ፡-

፩) ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራሉ፤

፪) በቦርዱና በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**5. Powers and Responsibilities of the Deputy Chairperson of the Board**

The Deputy Chairperson of the board shall;

1) Act on behalf of the Chairperson in his absence;
2) Carry out activities entrusted to him by the Chairperson and the Board.

**፮. የቦርዱ የስራ ቦታ**

የቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በሌሎች ቦታዎች ሊከፍት ይችላል፡፡

**6. Powers and Responsibilities of the Deputy Chairperson of the Board**

The Board shall have its Headquarters in Addis Ababa and may open branch offices in other places as necessary.

**፯. በጀት እና የሰው ኃይል**

ለቦርዱ ስራ አስፈላጊ የሆነውን የሰው ኃይል፣ በጀት እና ጽህፈት ቤት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሟላለታል።

**7 .Budget and Human Resources**

The human resource, budget and office space necessary for the Board to undertake its activities shall be provided by the Secretariat of the House of Peoples' Representatives.

**፰. የቦርዱ ምልዐተ ጉባኤ እና ውሳኔ አሰጣጥ**

፩) ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፪) የቦርዱ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናል።

፫) ድምጹ እኩል በኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የያዘው አቋም የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል።

**8 . Board Quorum and Decision Making**

1) The Board shall have a quorum if more than half of its members are present.
2) Decisions of the Board shall be passed by a majority vote of members present and voting.
3) In case of a tie, the vote of the Board Chairperson shall break the tie.

**፱. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

አዋጁ ከመጋቢት ፴ ቀን ፪ሺ፲፪ ቀን ፱ሺ፲፪ ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ወራት ተፈጻሚ ይሆናል።

**9 . Effective Date**

This Proclamation shall be effective for five months from 8th April 2020.

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

**Done at Addis Ababa On the April 16th Day of 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESDIENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**